# የኦዲት ግኝት መረጃ አመላካች

**መረጃ ሰጪው:** - የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

**ኦዲት ተደራጊ:** - የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

**ኦዲት የተደረገው የበጀት ዓመት:** - የ2013 2ኛ ሩብ ዓመት

**የኦዲት አካባቢ:** - የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት

**የኦዲት ግኝት:** -

## 1. ለግዢ ሥራ ለሠራተኞች በቅድሚያ ተከፍለው ሳይወራረዱ የቆዩ ሂሳቦች በድምሩ ብር 17,437.00

### 1.1 ሁኔታ

ለግዢ ስራ የሚውል ለሚመለከታቸው ለመ/ቤቱ የተለያዩ ሰራተኞች የቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ በሂሳብ ቁጥር 5217110 (Advance to staff-purchase) ከተመዘገቡት ውስጥ ክፍያው ከተፈጸመበት እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ (ታህሳስ 30/2013) ድረስ ያልተወራረደ በድምሩ ብር 17,437.00 መኖሩ፤

### 1.2 መስፈርት

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ን/አ 4ለ.

### 1.3 መንስኤ

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያን አለመረዳት፤ አክብሮ ተግባራዊ አለማድረግ፤ ወይም ቸልተኝነትን ማሳየት፤

### 1.4 የሚያስከትለው ጉዳት፣

ለመ/ቤቱ ጉዳይ ሲባል በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ ለተባለው ዓላማ በወቅቱ ስራ ላይ ላይውል ይችላል፣ ገንዘቡ ሳይወራረድ/ሳይሰበሰብ ለረዥም ጊዜ ሊቆይ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት በየጊዜው እየጨመረ ሊሄድ ይችላል፡፡

## 2. ለአቅራቢ ድርጅቶች በቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ ያልተወራረደ በድምሩ ብር 219,103.52

### 2.1 ሁኔታ፤

የተለያዩ ግዢዎችን መፈጸም እንዲቻል ለተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች በቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ በሂሳብ ቁጥር 5217205 (prepayment to suppliers) ተመዝግቦ እስከ ሁለተኛ ሩብ ዓመት መጨረሻ (ታህሳስ 30/2013) ዓ.ም ያልተወራረደ በድምሩ ብር 219,103.52 መኖሩ፤

### 2.2 መስፈርት፤

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ን/አ 4ለ እና የግዢ ትዕዛዝ፡፡

### 2.2 መንስኤ፣

እንዲገዙ የተጠየቁት ዕቃዎች በግዢ ትዕዛዙ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አቅራቢ ድርጅቶቹ እንዲያቀርቡ ግዢውን የሚከታተለው የመ/ቤቱ ሰራተኛ ብርቱ ክትትል አለማድረግና የፋይናንስ ቡድኑም የቁጥጥር ስራውን በማጠናከር ሂሳቡ በወቅቱ እንዲወራረድ ክትትል አለማድረግ፣

### 2.3 የሚያስከትለው ጉዳት፣

እንዲገዛ የተጠየቀው እቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢው ድርጅት በወቅቱ ላያቀርብ ይችላል፤ ገንዘቡ ተመላሽ ላይሆንና ለሌላ ጉዳይም ሊውል ይችላል፡፡

## 3. ተገቢውን የግዢ ዘዴ ባለመጠቀም የተፈጸመ በድምሩ የብር 203,722.00 ግዢ፣

### 3.1 ሁኔታ

አስቀድሞ በማቀድ እና ግልጽ የጨረታ ዘዴን ተጠቅሞ ግዢን መፈጸም ሲገባ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 203,722.00 የሆኑ የጽህፈትና የጽዳት ዕቃዎች እንዲሁም የእጅ ሰፍት ግዢዎችን በዋጋ ማቅረቢያ የግዢ ዘዴ ተጠቅሞ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸመ መሆኑ፤

### 3.2 መስፈርት

የፌደራል መንግስት የግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009 አንቀጽ 5(1) እና 8(መ)፣ የፌደራል መንግስት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀፅ 24.1 እና 24.8፣

### 3.3 መንስኤ

አዋጁንና የአፈጻጸም መመሪያውን አለመረዳት፤ አክብሮ ተግባራዊ አለማድረግ፤ ወይም ቸልተኝነትን ማሳየት፤

### 3.4 የሚያስከትለው ጉዳት

አዋጅንና መመሪያን ተከትሎ ግዢን አለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፣ የሀብት አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ ብቃትን ውጤታማነትን ሊያስገኝ በሚችል መንገድ የተፈጸመ ላይሆን ይችላል፤

**ኦዲት አድራጊው፤** <u>የመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት ቡድን</u>

**ያዘጋጀው፡** የሺጥላ ገ/ክርስቶስ

**ፊርማ፡**

**ቀን፡** 07/7/2013

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agricultural Transformation Agency

**ያጸደቀው፡** በላቸው በየነ

**ፊርማ፡**

**ቀን፡** 07/7/2013